


# 5

# ሥጋዊ ክርስቲያን

## 5-1

ሐዋርያው ጳውሎስ “…እኔ ከኃጢአት በታች ልሆን የተሸጥሁ የሥጋ ነኝ” ይላል። እንደገና የተወለደ በክርስቶስ ውስጥ ያለ ወይንም “ክርስቶስ በውስጤ አለ” ብሎ የሚያምን ክርስትያን ሥጋዊ መሆን እንዴት ይችላል? የሚል ጥያቄ በውስጣችን መፈጠሩ አይቀርም። ምክንያታችንም ሥጋዊ ከሆነ ክርስቲያን አይደለም፤ ከሆነ ደግሞ ሥጋዊ መሆን አይችልም በሚል ሃሳብ ላይ የተደገፈ ይሆናል። ይሁን እንጂ መጽሀፍ ቅዱስ ሥጋዊ ክርስትያን እንዳለ ያረጋግጥልናል። ክርስቲያኖች እንሁን እንጂ ገና ያልጸናን ልንሆን እንችላለን። በውስጣችን መንፈስ ቅዱስ ይኑር እንጂ በህይወታችን ሙሉ በሙሉ ክርስቶስን አናሳይም ይሆናል። ይህም እንዲህም ሊሆን ይቻለው እኛነታችን ስለቀደመ ክርስቶስን ሸፍነነዋል። ህይወታችን ከጥንቱ የሚለይበት ነገር ቢኖር በአሁኑ ጊዜ በሃይማኖት ካባ መሸፈናችን ብቻ ነው። “ሰውነት” የሚለው ቃል የመጣው ሳረክስ ከሚለው ከግሪክ ቃል ሲሆን፥ ትክክለኛ ትርጉሙ ሥጋ ማለት ነው። ጳውሎስ ሥጋ ብሎ የሚጠራው ከላይ ያለውን ቀፎ ሥጋዊ አካል ሳይሆን የሰውን ጠቅላላ ሁለንተና ማለቱ ነው። ጳውሎስ **“በስጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር አውቃለሁ”** ይላል ሮሜ 7፥18 ላይ። “እኔ” መጀመሪያ ክርስቶስ ሁለተኛ እስከሆነ ድረስ በክርስቶስ ውስጥ ብንኖርም አሁንም ሥጋውያን ነን።

## ሥጋዊ ክርስቲያን በምን ይለያል?

### ሀ. በእምነቱ ህጻን ነው

ወደ ክርስቶስ ገና በቀርቡ የመጣን ሰው ማየት ደስ ይላል። ህይወቱ ፍጹም ይባርካል። የሚታይበት የደስታ መልክ፤ ለጌታው ያለው ፍቅር፤ ደስ የሚያሰኝ ነው። ከአሥር ዓመትም በኋላ ያ አማኝ መጀመሪያ የነበረውን ዓይነት አቋም የያዘ ከሆነ ግን ይዞታው ከማስደስቱ ይልቅ አሳሳቢ ይሆናል። የመንፈሳዊ ህይወት ልምምዱ የጸሎት ህይወቱ ስለ እግዚአብሔር ያለው እውቀትና ግምቱ የመጻሐፍ ቅዱስ ችሎታው ገና መጀመሪያ ወደ ክርስቶስ ሲመጣ የነበረውን ዓይነት ከሆነ ያ አማኝ በእርግጥም በእምነቱ ህጻን ብቻ ሳይሆን ሥጋዊም ነው።

### ለ. በወተት ብቻ ይኖራል

ህጻን ከወተት ሌላ መመገብ አይችልም። ደቆ፣ ተፈጭቶና ተበጥብጦ ከላተሰጠው አኝኮ መዋጥ አይሆንለትም። “አሁንም ገና ህጻን ስለሆናችሁ ወተት ጋትኳችሁ” ይላል ጳውሎስ። አዎን በእምነቱ ገና ህጻን የሆነም ሰው በሌላ ሰው ድጋፍ ካልሆነ፣ ሌላው መጽሐፍ ቅዱስ ካላነበበለት ሌላው ሰው

ካልጸለየለት፣ ወደ ቤተክርስቲያን እንዲሄድ ካላደፋፈሩት፥ ራሱን ችሎ አይቆምም። አቅፋችሁ፣ ደግፋችሁ፣ አኝካችሁና በጥብጣችሁ ካልሰጣችሁኝ መቆም አልችልም ይላል። በእምነቱ ብዙ ዓመት ያቆየ ይሁን እንጂ ያ አማኝ አሁንም እንደ ህጻን በወተት መኖርን ይመርጣል። ድሮ ከሚያውቀው የበለጠ ጥንት ከተለማመደው ዓይነት የወጣ አዲስና ዕድገት ያለው ልምምድ ማየት አይፈልግም።

## ሐ. በመከፋፈል ያምናል

የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያን አማኞች "እኔ የጳውሎስ፣ እኔ የአጵሎስ ነኝ፣…እኔ የቀያፋ ነኝ" በማለት እርስ በርሳቸው ተከፋፈሉ። ጳውሎስም ይህን ሰምቶ ገና አሁንም ሥጋውያን መሆናቸውን ገልጾ ጻፈላቸው። ሥጋዊ ክርስቲያን "አንድ ሃሳብ፣ አንድ ልብ ይሁንላችሁ" የሚለው የወንጌል ቃል እንግዳ ሃሳብ ይሆንበታል። የሥጋዊ ክርስቲያን ዋና ምልክቱ በወንድማማች መካከል ጠብ በመዝራት መከፋፈ ልን ሲፈጥር ነው።

## መ. ክፉውንና ደጉን አይለይም

መጥፎ ሽታ ባለበት አካባቢ መኖር የለመደ ሰው ጥሩውን ከመጥፎ ሽታ ለይቶ ማወቅ አይሆንለ ትም። ልዩነትም እንዳላቸው መገንዘብ አይችልም። በዓለም ውስጥ እንደልባቸው የሚገቡና የሚወጡ ኃጢአትን ከጽድቅ መለየት ስለማይችሉ ኃጢአት ሲሠሩ ህሊናቸውን አይከብደውም። በዓለም ውስጥ ከሚታየው ኃጢአት የሚበልጥበት ዋናው ምክንያት ሥጋውያን ክርስቲያኖች ሁለት ዓይነት ህይወት ስለ ሚኖሩ ነው።

## ሠ. ግልጽ የሆኑ ምልክቶች

"የሥጋ ሥራም የተገለጠ ነው። እርሱም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣኦትን ማምለክ፣ ምዋርት፣ ጥል፣ ክርክር፣ ቅናት፣ አድመኛነት፣ መለያየት፣ መናፍቅነት፣ ምቀኝነት፣ መግደል፣ ስካር፣ ዘፋኝነት ይህንን የሚመስል ነው" ገላትያ 5፥19-21። እነዚህን ከላይ የዘረዘርናቸውን ኃጢአቶች በሕይወቱ የሚለማመድ ማንኛውም ክርስትያን ቢኖር አሁንም ሥጋዊ ነው። ጳውሎስ የገላትያንን ሰዎች "በመንፈስ ጀምራችሁ በሥጋ ትፈጽማላችሁን" ብሎ ይጠይቃቸዋል። እነዚህ የገላትያ ቤተክርስቲያን ምዕመናን ጥሩ ክርስትያ ኖች ለመሆን ብዙ ሙከራ ያደርጉ ነበር። ግን ምን ያደርጋል ሙከራቸው በራሳቸው ኃይል ስለነበረ መንፈሳዊውን ወደ ሥጋ ለወጡት። ማንኛውም መልካም ሀሳብ አሠራሩ ሥርዓትን የተከተለና ጥሩ ቢሆንም፥ አላማው ግን ራስን ለማስቀደም ከሆነ ከሥጋዊ አቋም ውጪ አይደለም።

**በሚቀጥለው ክፍል፥ ከሥጋዊ ክርስትና እንዴት ነፃ መሆን እንደምንችል እንመለከታለን።**

**የጌታ ጸጋና ሰላም ከእናንተ ጋር ይሁን። አሜን!**